# ፍትህና ዲሞክራሲ በሌለበት አገር አልኖርም በሚል ምክንያት ራሱን በእሳት አቃጥሎ የገደለው መምህር የኔሰው ገብሬ የቀብር ስነስርአት ተፈጸመ

ህዳር 5 ቀን 2004 ዓ/ም



በዋካ ከተማ ነዋሪ የነበረው የ34 አመቱ መምህር የኔሰው ገብሬ ራሱን ያቃጠለው፣ የወረዳዎ ባለስልጣናት በአንድነት ተሰባስበው በቅርቡ በዋካ የተፈጠረውን ችግር በሚወያዩበት ወቅት ነው።

” የታሰሩ ወጣቶች ይፈቱ፣ ችግራቸውና ጥያቄያቸው መልስ ያግኝ በማለት ለወረዳ ባለስልጣናት ጥያቄ ያቀረበው መምህር የኔሰው፣ ባለስልጣናቱ ከግቢ እንዲወጣ ሲጠይቁት ” እኔ ለዚህ ለማረቃ ወረዳ ህዝብ እራሴን አቃጥላለሁ፣ በእኔ መቃጠል ወጣቶች ይለፍላቸው” በማለት በእጁ የያዘውን ቤንዚን በማርከፍከፍ ራሱን ማቃጠሉን የአካባቢው ነዋሪ የሆነው ወጣት ጦና ሀይሉ ተናግሯል ።

የአካባቢው ባለስልጣናት በቂ ህክምና እንዳያገኝ በመከልከላቸው ህይወቱ ማለፉን ነዋሪዎቹ ገልጠዋል።

የአካባቢው ህዝብ በከፍተኛ ሀዘንና ቁጭት በቀብር ስነስርአቱ ላይ ለመገኘት ቢተምም ፣ ፖሊስ ከመምህሩ ቤተሰቦችና የተወሰኑ ቁጥር ካላቸው ታዋቂ ሽማግሌዎችና አዋቂዎች በስተቀር ፣ በስነስርአቱ ላይ ረብሻ ያስነሳሉ ተብለው የተገመቱ ወጣቶች እንዳይገኙ ከልክሎአል።

የአካባቢው ህዝብ በመምህሩ ሞት ከፍተኛ ሀዘን እና ቁጭት እንደተሰማ ነዋሪዎች በዋካ ከተማ ከወረዳና መብት ጥያቄዎች ጋር የተነሳው ጥያቄ ” ፍትሐዊ ቢሆንም፣ መንግስት ግን አስፈላጊውን መልስ ሊሰጥ አልቻለም” በሚል ምክንያት፣ የቶጫ ወረዳ አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ ፈቃዱ ወልደሩፋኤልና ፣ የዞኑ አቃቢ ህግ አቶ ከበደ ካሳ በራሳቸው ፈቃድ ስልጣናቸውን መልቀቃቸውን” መዘገባችን ይታወሳል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከመልካም አስተዳዳርና ከፍትህ እጦት ጋር በተያያዘ ህዝቡ ተደጋጋሚ እሮሮ በማሰማት ላይ መሆኑ ይታወቃል። በጉዳዩ ዙሪያ የወረዳውን ባለስልጣናት ለማግኘት ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም።